## ህጋዊ ስለሆነ እርዳታ አቅርቦት

የገንዘብ እርዳታ ለህጋዊ አገልግሎት ማለት ህጋዊ የሆነ ችግር ባጋጠምዎ ጊዜ ለቪክቶሪያ የህግ ነክ እርዳታ ሰጪ/Victoria Legal Aid ጠበቃ ወይም ለግል ጠበቃ ለመክፈል እንዲረዳዎ የሚሰጥ የገንዘብ እርዳታ መጠን ነው። ጠበቃ ማድረግ የሚችለው :

- ህጋዊ የሆነ ምክር መስጠት
- ስምምነት ላይ ለማድረስ መርዳት
- ህጋዊ የሆነ ስነዶችን ማዘጋጀት
- እርስዎን ወክሎ በፍርድ ቤት ቆሞ መከራከር ናቸው።

የገንዘብ እርዳታን ለማግኘት በርስዎ የገንዘብ አቅምና ባለብዎት ህጋዊ ችግር ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ነው። በአጠቃላይ የገንዘብ እርዳታው ለወንጀል ነክ ወይም ለቤተሰብ ጉዳይ በተመለከተ ይሆናል። ነገር ግን ለተወሰኑ ህዝባዊ ጉዳዮችም ማለት እንደ አድልዎ መፍጠር፣ የኢሚግሬሽን፣ ማህበራዊ ደህንነት ወይም የአእምሮ ጤንነት ጉዳይ በተመለከተም ሊሰጥ ይችላል።

የገንዘብ እርዳታው ሁልጊዜ ነጻ አይደለም። እርስዎ የሚከፍሉት መጠን ባለዎ የገንዘብ አቅም ሁኔታ ይወሰናል።

እንዴት እንደምረዳዎ ለማወቅ ደውሎ ማነጋገር ይችላሉ።

## አስተርጓሚ ለማግኘት

አስተርጓሚ ማግኘት ይችላሉ። ሲደውሉልን በሚናገሩት ቋንቋ አስተርጓሚ እንዲቀርብልዎ ይጠይቁ። በቪክቶሪያ ህጋዊ እርዳታ ሰጪ/Victoria Legal Aid ቢሮ በኩል ቀጠሮ ሲቀናጅ አስተርጓሚ እንዲቀርብልዎ መጠየቅ።

እንዲሁም ለትርጉምና ማስተርጎም አገልግሎት በቁጥር (Translating and Interpreting Service) 131 450 መደወልና ከቪክቶሪያ ህጋዊ እርዳታ ሰጪ/Victoria Legal Aid ጋር እንዲያገናኝዎ መጠየቅ ይችላሉ።

## ግላዊ መብትዎን መጠበቅና ማክበር

የርስዎን ግላዊ የሆነ መረጃ ህጉ ካላስገደደ በስተቀር ለማንም ሰው አሳልፈን አንሰጥም።

የደንበኞቻችንን ሚስጢራዊነት በሞላ እናከብራለን። ስለዚህ ከርስዎ ጉዳይ ጋር ግንኙነት ያለው ሰው ከዚህ በፊት ረድተን ከሆነ ልንሰጥዎ የምንችለው አጠቃላይ የሆነ መረጃ ብቻ ይሆናል። ሆኖም ወደ ሌላ ጠበቃ ወይም ህጋዊ ድርጅት ልንመራዎት እንችላለን።

## Our Legal Information Service

## (ህጋዊ መረጃ ሰጪ አገልግሎታችን)

ከሰኞ እስከ ዓርብ፣ ከጠዋቱ 8.45 am እስከ 5.15 pm ክፍት ነው።

በስልክ 9269 0120 ወይም በገጠር ሆኖ ለሚደውሉ 1800 677 402

Interpreter

ስለ አጠቃላይ ህግና እንዴት እንደምንረዳዎት ለማወቅ ያነጋግሩን። እንግሊዝኛ ወይም ሌላ ቋንቋ ከሚናገር ሰው ጋር ሊነጋገሩ ይችላሉ።

## ቢሮቻችን

ከሰኞ እስከ ዓርብ፣ ከጠዋቱ 8.45 am እስከ 5.15 pm ክፍት ናቸው።

እነሱም፣

| | |
|---|---|
| Bairnsdale | 5153 1975 |
| Ballarat | 5329 6222 |
| | በነጻ ለመደወል 1800 081 719 |
| Bendigo | 5448 2333 |
| | በነጻ ለመደወል 1800 254 500 |
| Broadmeadows | 9302 8777 |
| Dandenong | 9767 7111 |
| Frankston | 9784 5222 |
| Geelong | 5226 5666 |
| | በነጻ ለመደወል 1800 196 200 |
| Horsham | 5381 6000 |
| | በነጻ ለመደወል 1800 177 638 |
| Melbourne | 9269 0120 |
| Morwell | 5134 8055 |
| Preston | 9416 6444 |
| Ringwood | 9259 5444 |
| Shepparton | 5823 6200 |
| Sunshine | 9300 5333 |
| Warrnambool | 5559 7222 |
| | በነጻ ለመደወል 1800 651 022 |

በሁሉም ቢሮቻችን ለአካለ ስንኩሎች ምቹ መገልገያ የሚያቀርቡ ናቸው።

## ህዝባዊ የሆነ ቤተ መጽሐፍታችን

ከሰኞ እስከ ዓርብ፣ ከጠዋቱ 9 am እስከ 5 pm

አድራሻው፣ 350 Queen Street, Melbourne

## ድረ ገጻችን

www.legalaid.vic.gov.au

DLP-CO-AMH-0908

Printed on recycled paper

Do you have a legal problem?

Amharic

September 2008

# ህጋዊ የሆነ ችግር አለብዎት?

# Victoria Legal Aid



## ስለ ቪክቶሪያ ህጋዊ የሆነ እርዳታ ሰጪ/Victoria Legal Aid

**ወንጀል ነክ በሆኑ ጉዳዮች፣ የቤተሰብ መለያየት፣ በቤተሰብ ብጥብጥ፣ የልጅ ድጎማን፣ ስለ ኢሚግሬሽን፣ ስለ ማህበራዊ ዋስትና/ሶሻል ሰኩሪቲ፣ የአእምሮ መታወክ የአድልዎ መፍጠር፣ የቤት ኪራይን፣ እዳንና የትራፊክ ቅጣትን በተመለከተ ባለዎት ህጋዊ ችግር ላይ ልንረዳዎ እንችላለን።**

## አገልግሎታችን

ነጻ የሆነው ህጋዊ አገልግሎታችን ከዚህ በታች ያሉትን ያካትታል :

- በስልክ ላይ መረጃዎችን መስጠት
- አነስተኛ መጽሐፍት በማዘጋጀትና ትምህርታዊ መግለጫዎች መስጠት
- ህዝባዊ የህግ ቤተ መጻሐፍት
- በተወሰኑ ቋሚ ወይም ልዩ ፍርድ ቤቶች ምክር መስጠት ወይም ቀጠሮ መያዝ ናቸው።

እንዲሁም ለህግ ጠበቃ የሚሆን ገንዘብ አቅም ለሌላቸው ሰዎች ለጉዳዩ ማስፈጸሚያ የገንዘብ እርዳታ መስጠት እንችላለን።

## በስልክ ላይ ነጻ የሆነ ህጋዊ መረጃ አቅርቦት

ስለ ህግና እንዴት እንደምንረዳዎት በስልክ አጠቃላይ የሆነ መረጃ በነጻ ለማግኘት ለህጋዊ መረጃ አገልግሎታችን (Legal Information Service) ይደውሉ። ከሰኞ እስከ ዓርብ፣ ከጠዋቱ 8.45 am እስከ 5.15 pm ክፍት ነው።

ለከተማ ነዋሪዎች በስልክ ቁጥር (03) 9269 0120 ወይም ገጠር ነዋሪዎች 1800 677 402 ደውሉልን።

## ነጻ ህግ ነክ ትምህርት ለማህበረሰቡ፥

ስለ ህግና ስለ አገልግሎታችን የሚገልጹ ትናንሽ መጽሐፍት በእንግሊዝኛና በሌላ ቋንቋዎች የተዘጋጁ በነጻ እናቀርባለን። ጽሁፎችን በድረገጻችን ላይ ወይም በየትኛውም ቪክቶሪያ ህጋዊ የሆነ እርዳታ ሰጪ/Victoria Legal Aid ቢሮ ለማግኘት ይችላሉ።

ስለ ባልና ሚስት ፍችን በተመለከተ በነጻ ትምህርት መግለጫ አለን። ትምህርቱ የሚሰጠው በእንግሊዝኛ ቋንቋ ስለሆነ እንግሊዝኛ የማይረዳዎት ከሆነ ጓደኛዎትን ወይም ዘመድ እንዲያስተረጉምልዎ ይዘው መምጣት ይችላሉ።

Amharic

# ህጋዊ የሆነ ችግር አለብዎት?

Victoria Legal Aid

## ነጻ ህጋዊ የሆነ ምክር

የአገሪቱ ህግ እንዴት በርስዎ የህግ ችግር ላይ እንደሚጸናና እርስዎም ምን ማድረግ እንዳለብዎት የሚያነጋግሩ ጠበቆች አሉን።

ብዛት ባለው የህግ ነክ ችግሮች ነጻ ህጋዊ የሆነ ምክር እናቀርባለን። እነሱም :

- ወንጀል ነክ ጉዳዮች
- የቤተሰብ መለያየት
- የቤተሰብ ብጥብጥ
- ከባድ የትራፊክ ጥፋትና የህግ መጣስ ቅጣቶች
- የተወሰኑ ህዝባዊና ሰብዓዊ መብቶች ጉዳዮች ማለት እንደ ማህበራዊ ዋስትና/ሶሻል ሰኩሪቲ፣ የገንዘብ እዳ፣ የአእምሮ መረበሽ፣ ኢሚግሬሽንና ስደት፣ ሞግዚትነትና የአድልዎ መፍጠር ጉዳዮችን ያካተተ ይሆናል።

ስለ ገንዘብ ይዘት ወይም ንግድን በተመለከተ ጉዳይ ማለት ለቀረጥና ለንግድ፣ ንብረት ስለመግዛት፣ ሰለ ጡረታ መብትና ግንዛቤ ለማዳበር ለሚጠይቁ ሰዎች ሁሉ ህጋዊ የሆነ ምክር አንሰጥም።

ቀጠሮ ለማቀናጀት በዚህ ጀርባ ላይ ከተዘረዘሩትን በቪክቶሪያ ህጋዊ እርዳታ ሰጪ/Victoria Legal Aid ቢሮ ጋር ይገናኙ።

## ጠበቃዎች በፍርድ ቤት

**ወደ ፍርድ ቤት ችሎት ከመግባትዎ በፊት ህጋዊ የሆነ ምክር ማግኘቱ ጠቃሚ ነው።**

ስለዚህ ጠበቃ ከሌለዎት በቪክቶሪያ ውስጥ በብዙ ቋሚና ልዩ ፍርድ ቤቶች ጠበቆች አሉን።

የፍርድ ቤት ቀጠሮ ላላቸው ሰዎች በዚያኑ ቀን በነዚህ ' ተረኛ የህግ ጠበቃዎች ' በኩል እርዳታ ያገኛሉ። ምናልባትም እርስዎን በመወከል ቆሞ መከራከር ይችሉ ይሆናል።

እነዚህን ጠበቆች ለማየት ብዙ ሰዎች ይጠብቃሉ። ስለዚህ ምናልባት እርስዎ በጠየቁት ጊዜ ሁሉንም መርዳት አንችልም ይሆናል። ይሁን እንጂ ለአንዳንድ ሰዎችን በቅድሚያ መርዳት አለብን። ይኸውም :

- ጠንካራ ጉዳዮች ማለት እስር ቤት ያሉ ወደ ለመታሰር አስጊ ሁኔታ ላይ ያሉ
- ህጻናትን በሚመለከት ጉዳዮች
- ህጋዊ የሆነ እርዳታ ለማግኘት የገንዘብ አቅም ለሌላቸው
- ሰዎች ወደ ፍርድ ቤት ከመቅረባቸው በፊት ህጋዊ የሆነ እርዳታ ለማግኘት ያልቻሉትን ያካተተ ይሆናል።

ተረኛ ጠበቃ በቋሚው ወይም ልዩ ፍርድ ቤት ውስጥ ስለመኖሩ የፍርድ ቤት ሠራተኛ መጠየቅ ነው።

## ለቤተሰብ ጭቅጭቅ መፍትሄ አገልግሎት

በጠረጴዛ ዙሪያ ክርክር አመራር/Roundtable Dispute Management ሂደት የነጻ አገልግሎት ነው። በመለያየት ደረጃ ወይም በፍች መንገድ ላይ የሚገኙ ወላጆች ፍርድ ቤት ከመቅረብ ይልቅ የቤተሰብን ግጭቶቻቸውን ራሳቸው መፍትሄ እንዲሹላቸውና ለስምምነት እንዲደርሱ ይረዳቸዋል። እነዚህ ግጭቶች ምናልባት ስለ ወላጅነት፣ ስለ አሳዳጊነት፣ ስለ ድጋፍና ስለ ገንዘብ አዘገጃጀት ሊሆኑ ይችላል።

ይህንን አገልግሎት ለማግኘት ቢያንስ ከተጋጩ ቤተሰብ መካከል አንዱ ለህግ አገልግሎት የገንዘብ እርዳታ የሚያገኝ መሆን አለበት። በበለጠ መረጃ ለማግኘት እኛን ወይም የህግ ጠበቃን ያነጋግሩ።